# የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን

## መመሪያ ቁጥር 158/2011

የገቢዎች ሚኒስቴር

ግንቦት 2011 ዓ.ም

# የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን

## መመሪያ ቁጥር 158/2011

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን በጉምሩክ አዋጅ ከተደነገጉ መርሆዎችና ዘዴዎች ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ፣

የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ሥርዓት በተሻለ ደረጃ ዘመናዊ፣ ግልጽና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በወጥነት ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፣

የኮሚሽኑ የሥራ ክፍሎች፣ ቅ/ጽ/ቤቶች እና የጉምሩክ ኦፊሰሮች ከዋጋ አተማመን ጋር በተያያዘ የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወሰን በማስፈለጉ፣

አስመጪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በዋጋ አተማመን ረገድ የሚኖራቸውን መብትና የተጣለባቸውን ግዴታ ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የገቢዎች ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06(እንደተሻሻለው) አንቀፅ 180 (2) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 158/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ገቢ ዕቃ"** ማለት ወደ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የሚገባ ማንኛውም ዕቃ ማለት ሲሆን ገንዘብን አይጨምርም።

2) **"እርጅና ቅናሽ"** ማለት በተሽከርካሪው የኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ ላይ የአገልግሎት ዘመንን መሰረት በማድረግ በመቶኛ የሚደረግ ቅናሽ ሲሆን በሌሎች ዕቃዎች ላይ ወጥ የሆነ የመቶኛ ቅናሽ ነው።

3) **"የጉምሩክ ዋጋ"** ማለት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሲሆን በጉምሩክ አዋጅ እና በዚህ መመሪያ በተደነገጉት የዋጋ አተማመን ዘዴዎች አማካኝነት የሚሰላ እስከ

ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ወይም መውጫ ድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባው የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋና ሌሎች ወጪዎችና ክፍያዎች ጠቅላላ ድምር ነው፡፡

4) **"የማነፃፀሪያ ዋጋ"** ማለት በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የቀረበውን የዕቃ ዋጋ ትክክለኛነት ለማጣራት እና ለመወሰን የሚያገለግል በጉምሩክ ዳታ ቤዝ ዉስጥ ያለ እንዲሁም በጉምሩክ ተቀባይነት ያገኘ ወደ ኋላ የማስላት ዘዴ ፣ በሚዛናዊ ዘዴ፣ በወጪ ስሌት እና የዓለም አቀፍ የዋጋ መረጃን መሰረት በማድረግ የተገኘ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች ዋጋ መረጃ ነው፡፡

5) **"መነሻ ዋጋ"** ማለት የዕቃን ዋጋ አሳንሶ የማቅረብ ድርጊቶችን ለመከላከል ሲባል በሥጋት ሥራ አመራር መርህ መሠረት ከፍተኛ ሥጋት ባለባቸው የተመረጡ ዕቃዎች ላይ በጉምሩክ የሚደራጅ የዋጋ መረጃ ነው፡፡

6) **"የ ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ *(FOB Price)* ማለት"** የዕቃው የመሸጫ ዋጋ እና በላኪ አገር እስከ የመጨረሻ መጫኛ ቦታ (ወደብ) ድረስ ለዕቃው የተከፈለ ወይም የሚከፈል ወጪ ድምር ነው፡፡

7) **"የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ *(CIF price)* ማለት"** የዕቃው የመሸጫ ዋጋ እና በላኪ አገር እስከ መጨረሻ መጫኛ ቦታ ወይም ወደብ ድረስ ለዕቃው የተከፈለ ወይም የሚከፈል ወጪ እና ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የኢንሹራንስ፣ የማጓጓዣ፣ የማስጫኛ፣ የማውረጃ እና የመንከባከቢያ ወጪ ድምር ነው፡፡

8) **"የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት** *(Ethiopian Customs Valuation System[ECVS])"* ማለት በኮሚሽኑ ተቀባይነት ያገኙ የገቢ ወይም ወጪ እቃዎች ዋጋ መረጃን እና የዓለማቀፍ ዕቃዎች ዋጋ መረጃን መሠረት በማድረግ የሚደራጅ ለዋጋ ማነጻጸሪያነት የሚያገለግል የመረጃ ቋት ነው፡፡

9) **"በአንድ ሀገር የተመረቱ ዕቃዎች"** ማለት በአንድ ሉአላዊት ሀገር የተመረቱ ዕቃዎች ማለት ሲሆን በተፈጥሮ ወይም በቁፋሮ የተገኙ እቃዎችን ይጨምራል፡፡

10) **"በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ የሚገኙ አገሮች"** ማለት በአለም የንግድ ድርጅት ወይም በተባበሩት መንግስታት የአገሮች የእድገት ደረጃ ዝርዝር መሰረት በተመሳሳይ ዕድገት ደረጃ የሚገኙ አገራት ሲሆኑ የአህጉራዊ ነባራዊ ሁኔታንም ከግንዛቤ የሚያስገባ የአገራት ዝርዝርን ይጨምራል፡፡

11) **"ተቀራራቢ ዕቃ"** ማለት በአንድ አይነት ኢንዱስትሪ ወይም በአንድ አይነት የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመረቱ ዕቃዎች ማለት ሲሆን የአንድ ዓይነት እቃዎችና ተመሳሳይ ዕቃዎችን ይጨምራል፡፡

12) **"የአገር ውስጥ ገበያ ነጠላ መሸጫ ዋጋ"** ማለት ወደ አገር ውስጥ የገባው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ አገር ውስጥ የገቡና በገቡበት ሁኔታ በከፍተኛ ብዛት የተሸጠበት ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስን አይጨምርም፡፡

13) **"የጉምሩክ ዋጋ ማጣራት"** ማለት በሚመለከታቸው የጉምሩክ ባለሙያዎች አማካኝነት በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ዲክሌር የተደረገው የዕቃዎች ዋጋ ትክክለኛ የጉምሩክ ዋጋ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ወይም ለማጣራት ለዋጋው ወይም ለስሌቱ መነሻ የሚሆኑ ሰነዶችን የመመርመር ሂደት ነው፡፡

14) **"የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ** (Valuation Details Declaration (VDD))" ማለት ከዕቃ ዲክሌራሲዮን በተጨማሪ የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን የሚያስፈልጉ መግለጫዎችና መረጃዎችን በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ በዝርዝር ተሞልቶ ለኮሚሽኑ የሚቀርብበት የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ማሳወቂያ ሥርዓት ነው፡፡

15) **"የንግድ ደረጃ"** ማለት ሻጭ ድርጅቶች ባላቸው የንግድ ሸያጭ ሰንሰለት ቅደም ተከተል መሰረት የአንድ እቃ ዋጋ በአምራች፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ደረጃ ሊለያይ የሚችልበትን የንግድ ሁኔታ የሚያሳይ ደረጃ ነው፡፡

16) **"ተቀራራቢ አማካይ ዋጋ** /Weighted Average/" ማለት በተቀራራቢ ጊዜ ለአንድ አይነት ዕቃ ሁለትና ከዚያ በላይ የተለያዩ ዋጋዎች በሚኖሩበት ጊዜ የተለያዩ ዋጋዎችና የዕቃውን ብዛት ታሳቢ በማድረግ የሚሰላ አማካይ የዋጋ ስሌት ነው፡፡

17) **"ዳይሬክቶሬት"** ማለት የዋጋ ትመና እና ልማት ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

18) **"ኮሚሽን"** ማለት የጉምሩክ ኮሚሽን ሲሆን የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ይጨምራል፡፡

19) **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) ነው፡፡

20) በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላት እና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

1) ቀረጥና ታክስ በሚከፈልባቸው ወይም በማይከፈልባቸው ገቢና ወጪ ዕቃዎች፣
2) ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ከጉምሩክ ቁጥጥር ከተለቀቁ በኃላ በድጋሚ ቀረጥና ታክስ ለመሰብሰብ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምበት ሁኔታ ሲያጋጥም፣
3) ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው ከተለቀቁ በኂላ ኦዲት የሚካሄድባቸው ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም፣

4) የእርጅና ቅናሽስሌት አሰራር ሳይጨምር ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች እና በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ዋጋ አተማመን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ጉምሩክ ዋጋ አወሳሰን ሁኔታ

## ምዕራፍ አንድ

## የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ዘዴዎች አፈፃፀም

4. መርህ

የዕቃዎች የጉምሩክ ዋጋ በሚወሰንበት ጊዜ፡-

(ሀ) የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴን፤

(ለ) የአንድ አይነት ዕቃዎች ዋጋ አተማመን ዘዴን፤

(ሐ) የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አተማመን ዘዴን፤

(መ) ወደ ኋላ የማስላት አተማመን ዘዴን፤

(ሠ) በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ አተማመን ዘዴን እና

(ረ) ሚዛናዊ የዋጋ አተማመን ዘዴን በቅደም ተከተል በመጠቀም ይሆናል፡፡

5. የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ አፈፃፀም

1) ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ እቃ የግብይት ዋጋ ተደርጐ የሚወሰደው ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ለተሸጠው ዕቃ በትክክል የተከፈለው ወይም የሚከፈለው የግብይት ዋጋ ሲሆን በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች ታክለውበት ነው፡፡

2) በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ዋጋ *(Declared Value)* በቀጥታ ተቀባይነት የማይኖረው ወይም ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 90(1)(ሀ)-(መ) የተቀመጡት መስፈርቶች ካልተሟሉ እና/ወይም የዋጋ ትመና ኦፊሰሩ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንዱ አለ ብሎ ሲያምን ወይም ሲገምት ይሆናል፡-

   ሀ/ በዋጋ ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የዕቃው መግለጫዎች፣ የብዛት፣ የዓይነት፣ የጥራት፣ የመለኪያ፣ የምርት ሀገር፣ የምርት ዘመን መግለጫዎች እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ማስረጃዎች በትክክል ካልተገለጹ ወይም ካልቀረቡ፣

   ለ/ በሀሰት ወይም በተጨበረበረ መልኩ የተዘጋጀ ሰነድ/ማስረጃ የቀረበ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ካለው፣

ሐ/ በአዋጁ አንቀፅ 96 ላይ የተጠቀሱት ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የግብይት ዋጋ ውስጥ ካልተካተቱ ወይም ዋጋቸውን ለመተመን የሚያስችሉ ተጨባጭ ማስረጃዎችን ዲክላራሲዮን አቅራቢው ካላቀረበ፣

መ/ በዲክላሲዮን አቅራቢው የቀረበው የእያንዳንዱ የዕቃ ዋጋ እና በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታቤዝ ውስጥ የሚገኙ የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች አማካኝ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ በማነስ የንግድ ዕቃ አስመጪ ከ5% እንዲሁም የአምራች አስመጪ ድርጅት ከ10% በላይ ከሆነ፣

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲከሰቱ የሚከተሉት ተግባራት በቅደም ተከተል ይፈፀማሉ፡-

ሀ/ የጉምሩክ ባለሙያ ወይም ኃላፊው የዲክላራሲዮን አቅራቢውን ዋጋ የጠረጠረበትን ምክንያት በመግለጽ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በአካል ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም ስለ ዕቃው ዋጋ ትክክለኛነት የሚያስረዱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ይጠየቃል፣

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2(መ) የተመለከተው ሲያጋጥም በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የቀረበው የዕቃው ዋጋ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለዉ የቀረበው ዋጋ በዓለማቀፍ ደረጃ የታወቀ የዋጋ ለውጥ መኖሩን በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ለኮሚሽኑ ማቅረብና ማስረዳት ከቻለ እና በቅ/ጽ/ቤቱሥራ አስኪያ ጅ ወይም ስራ አስኪያጁ በሚወክለው የጉምሩክ ስራ ኃላፊ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡

ሐ/ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የተጠየቀውን ማስረጃ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (ሀ) ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ገደብ ካላቀረበ ባለሙያው ውሳኔውን በማሳወቅ በሚቀጥለው የዋጋ አተማመን ዘዴ የዕቃውን ዋጋ ወስኖ ያስከፍላል፡፡

## 6. በገዥና ሻጭ መካከል ግንኙነት አለ ተብሎ በሚጠረጠርበት ጊዜ ስለሚኖር አሰራር

1) የቅ/ጽ/ቤቱ የጉምሩክ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ከሻጭ ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑንና ግንኙነቱ በግብይት ዋጋው ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ከጠረጠረ በልዩነት ለሚፈለገው የቀረጥና ታክስ መጠን በቂ ዋስትና እንዲያቀርብ በማድረግ ቀጣይ ማጣራት እንዲደረግ ለዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት ያሳውቃል፡፡

2) ዳይሬክቶሬቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የቀረበለትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 7. በሻጭና በገዥ መካከል ግንኙነት ስለመኖሩ የሚደረግ ማጣራት

1) በሻጭና በገገር መካከል ግንኙነት ሲኖር ግንኙነቱ በቀረበው የዕቃ ዋጋ ላይ ተፅዕኖ ስለማሳደሩ ለማረጋገጥ፡-

   ሀ/ የዕቃው ዋጋ የተወሰነበት ሁኔታ በተለይ ዕቃውን በሚያመርተው የኢንዱስትሪ ዘርፍ በማንኛውም ነፃ የገበያ ውድድር ውስጥ ትክክለኛ ዋጋ በሚወሰንበት ሁኔታ የተወሰነ መሆኑን፣

   ለ/ ዋጋው የተወሰነው ከሻጩ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ገገሮች በተወሰነበት ሁኔታ መሆኑን፣

   ሐ/ የግብይት ዋጋው አጠቃላይ ዕቃውን ለማምረት የሚጠይቀውን ወጪ እና አምራቹ በተመሳሳይ ወቅት ተመሳሳይ ዕቃ በመሸጥ ከሚያገኘው ትርፍ ጋር የሚመጣጠን ትርፍ ሊያስገኝ የሚችል መሆኑን ማጣራት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 90 በተደነገገው መሰረት ግንኙነት ባላቸው አካላት መካከል በተደረገ ግብይት የቀረበው የዕቃው ዋጋ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

   ሀ/ በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች አለመኖራቸውን ሲረጋገጥ፣ ወይም

   ለ/ በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት ለሌላቸው ገገሮች የተሸጠ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ ለንግድ ዕቃ አስመጪ ከ5% እና ለአምራች አስመጪ ከ10% ያልበለጠ ከሆነ ወይም በአንቀጽ 5 (3) (ለ) መሰረት ተቀባይነት ካገኘ፤

   ሐ/ ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ ከተወሰነ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ ጋር ያለው ልዩነት ለንግድ ዕቃ አስመጪ ከ5% እና ለአምራች አስመጪ ከ10% ያልበለጠ ከሆነ ፣ ወይም

   መ/ በወጪ ስሌት ላይ የተመሰረተ የማስላት ዘዴ ከተወሰነ አንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች ጋር ያለው ልዩነት ለንግድ ዕቃ አስመጪ ከ5% እና ለአምራች አስመጪ ከ10% ያልበለጠ ከሆነ፣

3) ዳይሬክቶሬቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ያደረገዉ የማጣራት ሂደት ዉጤት በተመለከተ ለቅ/ጽ/ቤቱና ለዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ግንኙነት መኖሩ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ከማሳወቁ በተጨማሪ በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋት ውስጥ መረጃዉን እንዲመዘገብ ያደርጋል፤፤

4) ቅ/ጽ/ቤቱ ግንኙነት ያላቸውን አካላት አስመልክቶ የተሰጠውን የዋጋ ውሳኔ እና በዋጋ መረጃ ቋት የተመዘገበውን መረጃ መነሻ በማድረግ ዲክላራሲዮን አቅራቢው አንድ

አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በቀጣይ ከሻጩ ሲያስመጣ ሌላ የተለየ ሁኔታ ወይም መረጃ እስካልተገኘ ድረስ በዚሁ መሠረት ተመሳሳይ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 8. <u>የአንድ አይነት ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን ዘዴ አፈጻጸም</u> ፡-

1/ የዕቃውን ዋጋ በግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ መወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀጽ 91 በተደነገገው መሠረት ዕቃው ከመግባቱ በፊት በነበሩት 90 ቀናት ውስጥ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃ እና በተቀራራቢ ብዛት ወደ ሀገር ገብተው በነበሩና ግንኙነት ለሌላቸው ገገርዎች የተሸጡ የአንድ አይነት ዕቃዎች አስመልክቶ በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ በሚያቀርበው የዋጋ መረጃ በመነሳት የዋጋ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የግብይት ዋጋን መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀፅ 91 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት፡-

ሀ) ተመሣሣይ ንግድ ደረጃ ኖሯቸው ነገር ግን በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ፣

ለ) ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ኖሯቸው ነገር ግን በተቀራራቢ ብዛት የተሸጡ ወይም

ሐ) ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ያላቸውና በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ አንድ አይነት ዕቃዎችን የንግድ ደረጃው ወይም የብዛት ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ አንድ አይነት ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ አድርጎ መጠቀም ይቻላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ ለተጠቀሱት ማስተካከያው ሲደረግ በተጨማሪ የግብይት ዋጋው በአዋጅ አንቀጽ 96/1/ የተጠቀሱት ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዝ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትንና አንድ ዓይነት የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ ወጪ የተደረጉትን የማጓጓዣ ፣ የመጫን፣የማውረድ የአያያዝ የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

4/ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ዲክሌር ያደረገው የአንድ አይነት ዕቃዎች ዋጋ ተቀባይነት ካላገኘ በኮሚሽኑ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት ከሚገኘው የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋን በማነፃፀር ይወሰናል፡፡

5/ የዕቃዎች ማነጻጸሪያ ዋጋ በመረጃ ቋት ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ በሚገኝበት ወቅት የጉምሩክ ዋጋ ማነጻጸሪያ ተደርጎ የሚወስደው የንግድ ዕቃ ባህሪ ያላቸውንና ተቀባይነት ያገኙ ዋጋዎችን በሙሉ ተቀራራቢ አማካይ (Weighted Average) ተጠቅሞ በማስላት ይሆናል፡፡

6/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቀራራቢ (Weighted Average) አማካይ ሲሰላ የማነፃፀሪያ ዋጋዎች ከ30 በመቶ በላይ የተጋነኑ ወይም ያነሱ ዋጋዎች በስሌቱ ውስጥ እንዳይካተቱ ይደረጋል፡፡

## 9. የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን ዘዴ አፈጻጸም

1/ የዕቃው ዋጋ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 8 መሰረት ሊወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀጽ 92 በተደነገገው መሠረት ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክሌር ያደረገው ዕቃ ከመግባቱ በፊት በነበሩት 90 ቀናት ውስጥ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃ እና በተቀራራቢ ብዛት ወደ ሀገር ገብተው በነበሩ ግንኙነት ለሌላቸው ገገርዎች የተሸጡ የተመሳሳይ ዕቃዎችን አስመልክቶ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ በሚያቀርበው የዋጋ መረጃ በመነሳት የዋጋ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የግብይት ዋጋን መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀፅ 92 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት፡-

ሀ) ተመሣሣይ የንግድ ደረጃ ኖሯቸው ነገር ግን በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ፣

ለ) ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ኖሯቸው ነገር ግን በተቀራራቢ ብዛት የተሸጡ ወይም

ሐ) ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ያላቸውና በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ ተመሣሣይ ዕቃዎችን የንግድ ደረጃው ወይም የብዛት ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተመሣሣይ ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ አድርጎ መጠቀም ይቻላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ (2) የተጠቀሱት ማስተካከያዎች ሲደረጉ የግብይት ዋጋው በአዋጁ አንቀጽ 96 (1) የተጠቀሱትን ወጪዎች በተጨማሪነት የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓገው ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትንና ተመሳሳይ የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ ወጪ የተደረጉትን የማጓጓገ፣ የማስጫኛ፣ የማውረጃ፣ የመንከባከቢያ እና የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

4/ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ዲክሌር ያደረገው የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ የዕቃው ዋጋ በኮሚሽኑ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት ከሚገኘው የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ ጋር በማነፃፀር የሚወሰን ይሆናል፡፡

5/ የዕቃዎች ማነጻጸሪያ ዋጋ በመረጃ ቋት ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ በሚገኝበት ወቅት የጉምሩክ ዋጋ ማነጻጸሪያ ተደርጎ የሚወስደው የንግድ ዕቃ ባህሪ ያላቸውንና ተቀባይነት ያገኙ ዋጋዎችን በሙሉ ተቀራራቢ አማካይ (Weighted Average) ተጠቅሞ በማስላት ይሆናል፡፡

6/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቀራራቢ (Weighted Average) አማካይ ሲሰላ የማነፃፀሪያ ዋጋዎች ከ30 በመቶ በላይ የተጋነኑ ወይም ያነሱ ዋጋዎች በስሌቱ ውስጥ እንዳይካተቱ ይደረጋል፡፡

10. <u>ወደ ኋላ የማስላት ዘዴ አፈጻጸም</u>

1/ የዕቃው ዋጋ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ፣ 8 እና 9 መሰረት መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 93 በተደነገገው መሠረት የዕቃዎችን ዋጋ በሚሰላበት ጊዜ ግንኙነት በሌላቸው ገዢና ሻጭ መካከል በተደረገ ግብይት በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ወይም በሌሎች ዲክላራሲዮን አቅራቢዎች ዕቃው ከተጫነበት አገር በቀጥታ ወይም ከሌላ አገር ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወይም ወደ አገር ውስጥ ከገባ 90 ቀናት ያልበለጠው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በከፍተኛ ብዛት በሀገር ውስጥ በተሸጠበት ነጠላ ዋጋ ላይ በመመስረት እና በአዋጁ የተጠቀሱት ዝርዝር ወጪዎችና የትርፍ መጠን ከመሸጫ ዋጋው ላይ በመቀነስ ይወሰናል።

2/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል "ሻጭ" ማለት ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ሲሆን "ገዥ" ማለት ዕቃውን ከዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የገዛ ሲሆን እንደ ሁኔታው አከፋፋይ፣ ቸርቻሪ ወይም የመጨረሻ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

3/ በዚህ አንቀጽ በተደነገገው ዘዴ መሠረት የጉምሩክ ዋጋ ሊተመን የሚችለው፡-

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ 90 በተደነገገው መሰረት በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ (ሻጩ) እና በገዢው መካከል ግንኙነት ከሌለ ወይም ግንኙነቱ በመሸጫ ዋጋው ላይ ተጽዕኖ እንዳላሳደረ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ማስረጃ ማቅርብ ከቻለ፣

ለ) በገዢ በኩል ለሻጩ ከእቃው ጋር በተያያዘ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በነፃ ወይም በቅናሽ ዋጋ የተከፈለ ክፍያ ወይም የተሰጠ ስጦታ ከሌለ፣ እና

ሐ) ዕቃው በከፍተኛ ብዛት በአገር ውስጥ የተሸጠበት ነጠላ ዋጋ መሆኑን በማስረጃ ማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ነው።

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የዕቃው ዋጋ የሚሰላው ከዚህ በታች የተገለጹትን ቀመሮች መሰረት በማድረግ ይሆናል።

ሀ) ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በገባበት ሁኔታ ከተሸጠ የጉምሩክ ዋጋው እንደሚከተለው ይሰላል።

(1) DPV (Customs Value CIF in ETB) **DMP – (CPS + DGEx + TDT)**

(2) FOB Price ( in USD) = DPV (CIF in USD) - IFO

ለ) ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ከገባ በኋላ ቀጣይ የምርት ሂደት ተከናውኖበት የተሸጠ እንደሆነ የጉምሩክ ዋጋው በሚከተለው ሁኔታ ይሰላል፤

(1) DPV (in ETB) = DMP — (CPS + DGEx + TDT + DVA)

(2) FOB Price ( in USD) = DPV (CIF in USD) - IFO

**መፍቻ**

DPV = የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ (Duty Paying Value - Customs Value)
DMP = የሀገር ውስጥ ገበያ መሸጫ ነጠላ ዋጋ (Domestic Market Selling Unit Price)
FOB = የዕቃ ዋጋ እስከ ወደብ ድረስ/Free on Bord/
CIF = የዕቃ ዋጋ፣ የማጓጓዣ ወጪ እና የኢንሹራንስ አረቦን ወጪ (Cost, (Freight and Insurance)
CPS = ከሽያጭ የተገኘ ኮሚሽን ወይም ትርፍ መጠን (Commission or Profit from Sale)
DGEx = ሀገር ውስጥ የሚከፈሉ አጠቃላይ ወጪዎች መጠን (Domestic General Expenses)
TDT = አጠቃላይ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ መጠን (Total customs Duties and Taxes)
DVA = ዕቃው አገር ውስጥ ከገባ በኋላ በምርት ሂደት የተገኘ ተጨማሪ እሴት መጠን (Domestic Value Additions)
IFO = ዕቃው አገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት የተከፈለ የኢንሹራንስ፣ የመጓጓዣ ወጪ እና ሌሎች ወጪዎች መጠን (Insurance, Freight and Other Costs)
**ETB** = Ethiopian Birr

## 11. በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ የዋጋ አተማመን ዘዴ አፈጻጸም

1/ የዕቃዎች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 94 በተደነገገው መሠረት ለማስላት በዕቃው ዋጋ የሚካተቱ ለዕቃው የተከፈሉ ወይም የሚከፈሉ ክፍያዎችና ወጪዎችን ከአምራቹ ድርጅት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚገኙት መረጃዎች እና ደጋፊ ማስረጃዎች በመመርኮዝ ሊወሰን ይችላል፣

2/ በአዋጁ አንቀጽ 94 መሠረት ለመወሰን በላኪው ሀገር ተቀራራቢ የዕድገት ደረጃ ተመሳሳይ ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ ወይም በዕቃው ንግድ ዘርፉ አብዛኛውን ጊዜ ያለው የተለመደ ወይም አማካይ የመሸጫ፣ የማሸጊያና ሌሎች ወጪዎች እና የትርፍ መጠን ማስረጃ ላይ በመመርኮዝ ሊወሰን ይችላል።

## 12. ሚዛናዊ የዋጋ አተማመን ዘዴ አፈጻጸም

የዕቃዎች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 94 በተደነገገው የዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 8 እስከ 11 የተጠቀሱትን የዋጋ ትመና ዘዴዎችን በቅደም ተከታላቸው አተረጓጎማቸውን በማስፋት በአዋጁ ከተደነገገው አጠቃላይ መርህ ጋር የተጣጣመ ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ወቅታዊ መረጃ መሰረት ከዚህ በታች በተገለጸው አግባብ በቅደም ተከተል ዋጋ ይወሰናል።

**1/ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ሚዛናዊ ዘዴ፡-**

ሀ) በ90 ቀናት ውስጥ የገባ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ በማይገኝበት ወቅት በ180 ቀናት ውስጥ ወደ ሀገር የገባ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ እንደ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሊያገለግል ይችላል።

ለ) የዕቃዎች ማነጻጸሪያ ዋጋ በመረጃ ቋት ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ በሚገኝበት ወቅት የጉምሩክ ዋጋ ማነጻጸሪያ ተደርጎ የሚወሰደው የንግድ ዕቃ ባህሪ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

ያላቸውንና ተቀባይነት ያገኙ ዋጋዎችን በሙሉ ተቀራራቢ አማካይ (Weighted Average) ተጠቅሞ በማስላት ይሆናል፡፡

ሐ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቀራራቢ (Weighted Average) አማካይ ሲሰላ የማነፃፀሪያ ዋጋዎች ከ30 በመቶ በላይ የተጋነኑ ወይም ያነሱ ዋጋዎች በስሌቱ ውስጥ እንዳይካተቱ ይደረጋል፡፡

መ) ወደ አገር የገባው ዕቃ በተመረተበት አገር የተመረተ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ በማይገኝበት ጊዜ በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ በሚገኝ አገር የተመረተ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ አድርጎ መውሰድ ይችላል፡፡

ሠ) ወደኋላ በማስላት እና በወጪ ስሌት ላይ በተመሰረተ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት የተወሰኑ የአንድ አይነት ዕቃ ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ረ) በ180 ቀናት ውስጥ ወደ ሀገር የገባ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ ካልተገኘ ከ180 ቀናት በላይ በየስድስት ተጨማሪ ወራት ጊዜ ውስጥ ያለ መረጃ በቅደም ተከተል በመውሰድ ዋጋ መወሰን ይቻላል፡፡

2/ ወደ ኋላ የማስላት ሚዛናዊ ዘዴ ፡-

ሀ) በብዛት የተሸጠበት ዋጋ ካልተገኘ በነጠላ የተሸጠበትን አማካኝ ዋጋ እንደመነሻ በመውሰድ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) በተቀመጠው ቀመር መሰረት አስፈላጊውን ተቀናሾች በመቀነስ የጉምሩክ ዋጋ ይሰላል፣

ለ) ተጨባጭና ሊለኩ የሚችሉ መረጃዎች ማግኘት በማይችልበት ጊዜ ቀጥሎ ያሉትን ቀመሮች እንደ ቅደም ተከተላቸው በመጠቀም የCIF እና የFOB ዋጋን መወሰን ይቻላል፡፡

1] DPV (Customs Value CIF in ETB) =

$$\frac{DMP\,(1-pfm-exp)}{1+\sum taxrates}$$

2] FOB Price ( in USD) = DPV (CIF in USD) - IFO

**መፍቻ፡-**

DPV = የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ (Duty Paying Value - Customs Value)
DMP = የሀገር ውስጥ ገበያ መሸጫ ነጠላ ዋጋ (Domestic Market Selling Unit Price)
FOB = የዕቃ ዋጋ እስከ ወደብ ድረስ/Free on Bord/
CIF = የዕቃ ዋጋ፣ የማጓጓዣ ወጪ እና የኢንሹራንስ አረቦን ወጪ (Cost, (Freight and Insurance)



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

*pfm* = ከዕቃው ጠቅላላ ሽያጭ የሚገኝ የትርፍ ምጣኔ በመቶኛ (*percentage rate of usual Commissions or profits from sale of such goods)*

Exp = ከዕቃው ጠቅላላ ሽያጭ ታሳቢ የሚደረግ አጠቃላይ የወጪ ምጣኔ በመቶኛ (percentage (rate) of usual domestic general expenses in sale of such goods) tax rates = ለዕቃው የሚከፈለው ጠቅላላ (Cumultative Summation) የቀረጥና ታክስ ምጣኔ ስሌት

CIF in USD = CIF in ETB ሲካፈል በወቅቱ ባለው የገንዘብ ምንዛሬ መጠን

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) በተመለከተው ቀመር መሰረት የCIF ዋጋን ለማግኘት በገበያ ጥናት ከተገኘው የመሸጫ ዋጋ ላይ የሚከተሉት ሂሳቦች ተቀናሽ ይደረጋሉ፡፡

(1) ለጅምላ ሽያጭ (አስመጪ ቀጥታ ሽያጭ) 15% እና ለችርቻሮ ሽያጭ 30% ትርፍ ተቀናሽ፣

(2) ለጅምላ (አስመጪ ቀጥታ ሽያጭ) ሽያጭም ሆነ ለችርቻሮ ሽያጭ አጠቃላይ ወጪ 9%፣

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) በተመለከተው ቀመር መሰረት የተገኘውን የFOB ዋጋ ከኢንቮይስ የFOB ዋጋ ለማነፃፀር ዲክላራሲዮን አቅራቢው እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለኢንሹራንስ፣ ማጓጓዣ እና የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያ ወጪዎች የተከፈለበትን ማስረጃ ካላቀረበ ወይም ተቀባይነት ካላገኘ በቀመሩ ላይ የኢንሹራንስ ወጪ (2%)፣ የትራንስፖርት ወጪ (5%) እና የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያ ወጪዎች (5%) በድምሩ 12% ከኤፍ.ኦ.ቢ / FOB/ **ዋጋው** በመቀነስ ማስላት ይቻላል፡፡

ሠ) የገበያ ጥናት በሚደረግበት ወቅት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡

(1) ለማነፃፀሪያ የሚወሰደው ዕቃ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ እቃ መሆኑን ማረጋገጥ፣

(2) ዕቃው በአገር ውስጥ ሲሸጥ ወደ ሀገር ውስጥ በገባበት ይዞት መሆን ያለበት ሲሆን ተጨማሪ እሴት የታከለበት እንደሆነ ይህንኑ መጠን በተጨባጭ ማስረጃ ሊታወቅ ይገባል፣

(3) በአገር ውስጥ ሲሸጥ ግንኙነት በሌላቸው ገዢና ሻጭ መካከል የተደረገ ግብይት መሆን አለበት፣

(4) ዕቃዎች በከፍተኛ ብዛት በሀገር ውስጥ በተሸጡበት የጅምላ ወይም ነጠላ ዋጋ ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል፣

(5) ዕቃው የተሸጠበት ጊዜ ዕቃው በገባበት ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፣

(6) በገዢው በኩል ለሻጩ ከዕቃው ጋር በተያያዘ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ በነፃ በቅናሽ ዋጋ የተከፈለ ወይም የተሰጠ ስጦታ መኖር የለበትም፡፡

(7) ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለዕቃው፣ ለአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የተሸጠበትን የጅምላ ወይም የችርቻሮ ዋጋ በደረሰኝ የሚያቀርብ ከሆነ እና የቀረበው ደረሰኝ በትክክል የተሸጠበት መሆኑ ከተረጋገጠ ገበያ ከማጥናት ይልቅ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንደመነሻ ይወሰዳል፡፡

(8) ጥናቱን የሚያደርገው ቅ/ጽ/ቤት ወይም የሥራ ክፍል ዕቃው በብዛት የሚሸጥበትን ወይም አገልግሎት ላይ የሚውልበትን ቦታ ለይቶ ማጥናት አለበት.

(9) የዕቃው ዋጋ ከፍትሃዊነት አንፃር እና ኢኮኖሚውን ያገናዘበ ቦታ ላይ የገበያ ጥናቱ ማጥናት አለበት.

(10) ብዛት ያላቸው የተለያዩ አማራጭ ገበያዎች የሚገኙ ከሆነ የገበያ ጥናቱ የመጨረሻ አማካይ ውጤት ከመወሰዱ በፊት ዕቃው ቢያንስ ከሦስት ዕቃው በብዛት የሚሸጥበት ገበያ ወይም ድርጅቶች ተጠይቆ በብዛት የሚሸጥበትን አማካይ የዋጋ መረጃ መወሰድ አለበት፡፡

ረ) የገበያ ጥናት በሚደረግበት ወቅት ጥናቱን የሚያደርገው የሥራ ክፍል በዚህ መመሪያ አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ቅጽ የተመለከቱትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ጥናቱን ማከናወን ይኖርበታል፡፡

ሰ) ቅ/ጽ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ በተጠቀሰው የወደ ኋላ ሚዛናዊ ዘዴ በመጠቀም ያስተላለፈው ውሳኔ ውሳኔውን በተሰጠበት በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ከዝርዝር ማስረጃዎቹ ጋር ለዳይክቶሬቱ ማሳወቅ አለበት፣

**3/ ከድብልቅ ማቴሪያሎች የተሰሩ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን፡-**

ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ ከድብልቅ ማቴሪያሎች የተሰሩ ዕቃ ሆነው ቅ/ጽ/ቤቱ የጉምሩክ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ በሁሉም የዋጋ አተማመን ዘዴዎች በመጠቀም ውሳኔ መስጠት በማይችልበት ጊዜ የዕቃውን የጉምሩክ ዋጋ ለመወሰን ዕቃው የተሠራበት የድብልቅ ንጥረ ነገሮቹ ዋጋ ተወስዶ አማካይ ሬሾ ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡

* በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ገቢዎች ሚኒስቴር No. 1 ... Democratic ... of Ethiopia Ministry of Revenues

## ምዕራፍ ሁለት

## በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ስለሚጨመሩ፣ ስለሚቀነሱ እና የማይካተቱ ክፍያዎችና ወጪዎች አጠቃላይ አፈጻጸም ሂደት

13. በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ስለሚካተቱ ተጨማሪ ክፍያዎችና ወጪዎች

በአዋጁ አንቀጽ 96 በተደነገገው መሠረት እቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ ለዕቃው የተከፈሉ ወይም የሚከፈሉ ወጪዎችና ክፍያዎች በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መካተት አለባቸው፡፡

14. ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የግብይት ዋጋ ውስጥ የሚካተቱበት ሁኔታ፣

1/ በአዋጁ አንቀጽ 96 በተደነገገው መሠረት ተጨማሪ ወጪዎችና ክፍያዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ይካተታሉ፡-

ሀ) በኢንቮይሱ እና ሌሎች የንግድ ሰነዶች ላይ በግልጽ የተካተቱ ስለመሆናቸው ያልተገለጸ ከሆነ፣ ወይም

ለ) የተከፈለው የዕቃው ዋጋ በንግድ ሰነድ ላይ በትክክል ያልተገለፀ ከሆነ፣ ወይም

ሐ) ዋጋ ሊተመንበት ከቀረበው ዕቃ ጋር በተያያዘ የተከፈለ ሲሆን፤ ወይም

መ) ስለመከፈላቸው ግልጽ መረጃ የቀረበላቸው ከሆነ ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ እንዲካተቱ ሲደረግ፡-

ሀ) ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ በትክክል የተከፈሉት ወይም የሚከፈሉት ወጪዎችና ክፍያዎች በአስመጪው እንዲቀርብ በማድረግ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

ለ) በዲክራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የክፍያ ማስረጃ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ወይም በተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች መቅረብ ያልቻለ እንደሆነ በተመሳሳይ ጊዜ ከተመሳሳይ ሀገር የገባን አንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ለማጓጓዝ በተከፈለ ወጪ መሠረት ይወሰናል፡፡

ሐ) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ከጎረቤት ሀገራት ወደቦች እስከ መድረሻ የጉምሩክ ጣቢያ ላለው ርቀት የሚከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ከወደብ እስከ መግቢያ በር ያለዉ ርቀት ከወደብ እስከ መድረሻ ጣቢያው ላለው ርቀት ተካፍሎ የሚገኘው ውጤት ጠቅላላ በተከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ተባዝቶ የሚገኘው ውጤት ነው፡፡

ረ) ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የሮያሊቲ ክፍያ የሚፈፀምበት ሆኖ ሲገኝ ክፍያው አስመጪው ከላኪው ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ወይም በተሸጠ ጊዜ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

ሰ) የሮያሊቲ ክፍያው ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ያልተከፈለ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ረ) መሰረት መከፈል ያለበትን የሮያሊቲ ክፍያ የዕቃው ሽያጭ በተከናወነ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስመጪው አሳውቆ መክፈል አለበት፡፡

ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ረ) እና (ሰ) የተመለከተው ቢኖርም በሮያሊቲ ክፍያ ላይ ቀረጥና ታክስ ያልከፈለ አስመጪ ዕቃው ወደ አገር ውስጥ በገባ በአንድ ዓመት ውስጥ ጊዜ ውስጥ ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፤

ቀ) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የሚጨመሩ ክፍያዎች በተጨባጭ መረጃ መሠረት መተምን ባልተቻለ ጊዜ ኮሚሽኑ ወጪዎችንና ክፍያዎችን አግባብነት ካላቸው ከመንግስትና የግል መ/ቤቶች በሚያገኘው መረጃ መሰረት ዋጋ ሊተምን ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ተጨማሪ ክፍያዎች በተጨባጭ መረጃና ማስረጃ መተመን ባልተቻለበት ጊዜ ተጨማሪ ወጪዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት ይወሰናሉ፡-

ሀ) ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘው የዕቃው ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ላይ አምስት በመቶ በመውሰድ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል፡፡

ለ) ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያ ወጪዎችና ክፍያዎች ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘው የዕቃው ኤፍ.ኦ.ቢ /FOB/ ዋጋ ላይ አምስት በመቶ በመውሰድ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል፡፡

ሐ) ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የኢንሹራንስ ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘው የዕቃው ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ላይ ሁለት በመቶ በመውሰድ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል፡፡

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) የተመለከቱት ድንጋጌዎች በአየር ተጓጉዘው ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጡ ዕቃዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

4/ ከስሪት አገራቸዉ ዉጭ ከጎረቤት አገሮች የሚከናወኑ ግዥዎችን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 በተደነገገዉ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 15. በግብይት ዋጋ የማይካተቱ ክፍያዎች

1/ ለዕቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ውስጥ ተለይተው እስከተቀመጡ ድረስ የሚከተሉት ክፍያዎች በግብይት ዋጋ ውስጥ አይካተቱም፤

ሀ) የፋብሪካ መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች ወይም መሳሪያዎች ወደ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለተከናወነ ወይም ለሚከናወን የግንባታ፣ የማሻሻያ፣ የተከላ ወይም የጥገና ሥራ ወይም ለቴክኒክ ድጋፍ የሚከፈል ክፍያ፤

ለ) ዕቃዎች ወደ ጉምሩክ ክልል ከገቡ በኋላ የሚከፈል የትራንስፖርት ክፍያ፤

ሐ) ወደ አገር ውስጥ ከገቡት ዕቃዎች ግዥ ጋር በተያያዘ ገገርው ለገባው የብድር ወይም የፋይናንስ ስምምነት የሚከፈል የወለድ ክፍያ፤

መ) የግገር ኮሚሽን፤

ሠ) ወደ አገር ውስጥ ከገቡ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከፈለ ቀረጥ፣ ታክስና ሌሎች ክፍያዎች።

2/ የግብይት ዋጋ ሲወሰን የሚከተሉት ክፍያዎች ለዕቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ላይ አይደመሩም፤

ሀ) ወደ አገር ውስጥ የገቡትን ዕቃዎች በአገር ውስጥ እንደገና ለማምረት የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

ለ) ዕቃዎቹን ለመላክ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ ካልሆነ በስተቀር ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ለማከፋፈል ወይም እንደገና ለመሸጥ በገገርው የሚከፈሉ ክፍያዎች።

## 16. ከግብይት ዋጋ ላይ ስለሚቀነሱ ሂሳቦች

1/ ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ላይ የሚከተሉት ሂሳቦች ተቀናሽ ይደረጋሉ፡-

ሀ) ዕቃዎቹ በጉዞ ላይ ሳሉ የደረሰ ጉዳት በሚመለከተው ህጋዊ አካል ማስረጃው ተረጋግጦ ሲቀርብ፤

ለ) ዕቃዎቹ በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ሳሉ የደረሰ ጉዳት በሚመለከተው ህጋዊ አካል ማስረጃው ተረጋግጦ ሲቀርብ፤

ሐ) አደገኛ በመሆኑ ምክንያት እንዲቃጠል ወይም በሌላ አኳኋን እንዲወገድ የተደረገ ዕቃ ዋጋ።

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ (1) የተደነገገው ተፈፃሚ የሚሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው አስፈላጊ መረጃዎችና ማስረጃዎች ከዲክላራሲዮኑ ጋር በማያያዝ እና ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ ለኮሚሽኑ ሲያቀርብ እና ትክክለኛነቱ ሲረጋገጥ ነው።

## 17. ያገለገለ ዕቃ

ማንኛውም ያገለገለ ዕቃ ተሽከርካሪን ጨምሮ ወደ አገር ውስጥ በሚገባበት ጊዜ ቀረጥና ታክሱን ለመወሰን ምንም ዓይነት የእርጅና ቅናሽ አይደረግም፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት እና የመነሻ ዋጋ የሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች ማደራጀት

## 18. የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት አደረጃጀትና አጠቃቀም

1) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ኮሚሽኑ ወይም የሚመለከተው የኮሚሽኑ ባለሙያ በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች ዋጋቸው ትክክለኛ የግብይት ዋጋ ስለመሆኑ ለማጣራት እና ተገቢውን የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ለመወሰን የተዘጋጀውን የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት መጠቀም አለበት፡፡
2) የዋጋ መረጃ ስርዓት ዋጋን በማጣራት ሂደት እና በድህረ-እቃ አወጣጥ ኦዲት እንዲሁም በሌሎች አግባብነት ባላቸው የኮሚሽኑ ሥራዎች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡
3) ኮሚሽኑ በዋጋ መረጃ ዳታቤዝ የሚገኙ መረጃዎችን የዲክላራሲዮን አቅራቢዎችን ምስጢር በጠበቀ ሁኔታ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እና ሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ጋር የመረጃ ልውውጥ ሊያደረግ ይችላል፡፡
4) የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት ውስጥ በመግባት የሚችለው የይለፍ ቃል የተሰጠው ሰው ብቻ ነው፡፡

## 19. የመነሻ ዋጋ ስለሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች

1) በዚህ መመሪያ የተደነገገው ቢኖርም የጉምሩክ ዋጋን ወይም የኢንቮይስ ዋጋን አሳንሶ የማቅረብ ድርጊትን ለመከላከል የኮሚሽኑ ዋና መ/ቤት በየወቅቱ የዕቃዎች የመነሻ ዋጋ በማዘጋጀት የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ውሳኔ በመስጠት ያስፈጽማል፡፡
2) ኮሚሽኑ ከአጠቃላይ የዋጋ አተማመን መርህ ጋር በሚጣጣም መልኩ የንግድ መጠን የሌላቸው የግል መገልገያ ዕቃዎች ጨምሮ ሌሎች የመነሻ ዋጋ የሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች እንደአስፈላጊነቱ ዝርዝር በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፡፡
3) የመነሻ ዋጋ የሚቀመጥላቸው እቃዎች ዋጋቸው ከጉምሩክ ዋጋ መረጃ ጋር በሚነፃፀርበት ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) (መ) እና አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ)፣(ሐ) እና (መ) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንባቸውም፡፡

## 20. ከስሪት ሀገራቸው ውጪ ከጎረቤት ሀገራት ተገዝተው የሚገቡ እቃዎችን ዋጋ ስለመወሰን

ከስሪት ሀገራቸው ውጪ ከጎረቤት ሀገራት ተገዝተው የሚገቡ እቃዎች ዋጋ ሲወሰን፡-

1) በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የጎረቤት አገር ኤፍ.ኦ.ቢ. /FOB/ ዋጋ ከስሪት ሀገራቸው ተገዝተው ከገባው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በጉምሩክ የመረጃ ዋጋ ስርዓት ውስጥ የተያዘው የማነጻጸሪያ የሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እኩል ሆኖ ወይም በልጦ ከተገኘ የጎረቤት አገር ኤፍ.ኦ.ቢ. /FOB/ ዋጋ እንደ ሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ ተደርጎ በመውሰድና እስከ ሀገሪቱ የመግቢያ በር ድረስ ለዕቃው የተከፈለውን የየብስ መጓጓዣ ወጪ በማካተት ሊስተናገድ ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በዲክሌራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ ከሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር አንሶ ከተገኘ ዕቃው ከተመረተበት አገር ሲገዛ ባለው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ መሠረት እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡

## 21. የዓለማቀፍ ዋጋ መረጃ ምንጮች ስለ መጠቀም

1) የኮሚሽኑ ዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ሥርዓት ውስጥ በኮሚሽኑ ተቀባይነት ያገኙ የገቢ ዕቃዎች ዋጋ ማነፃፀሪያ ያልተገኘ እንደሆነ ወይም በሚገኘው መረጃ መሠረት ውሳኔ መስጠት ያልተቻለ እንደሆነ የተመረጡ ዓለም አቀፍ የዋጋ መረጃ ምንጮችን በመጠቀም የዕቃ ዋጋን መወሰን ይችላል፡፡
2) የኮሚሽኑ የዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት ከታወቁ ዓለም አቀፍ የዕቃ ዋጋ አቅራቢ ድርጅቶች ወይም ከተመረጡ ድህረ ገጾች በግዥ እና/ወይም ሌሎች መንገዶችን ወይም ከሀገራት ጋር በሚኖር የዕቃዎች ዋጋ መረጃ ልውውጥ ስምምነትን ወይም ሌሎች የዋጋ መረጃ ምንጮችን መሰረት በማድረግ የዋጋ መረጃ ቋቱን ያለማል፣ ይወስናል፣ ያስወስናለ፡፡
3) ኮሚሽነሩ ወይም የጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ኮሚሽነር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የሚሰጡ ውሳኔዎች የመከታተል፣የማረጋገጥ፣የማረም፣ የማሻሻል ህጋዊ መሆኑን ካረጋገጡ የተለዩ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ

### 22. የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ አቀራረብ

1/ ማንኛውም ዲክላራሲዮን አቅራቢ በአዋጁ አንቀጽ 10 (1) መሰረት ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ ሲያስገባ አስፈላጊ መረጃዎችን በዋጋ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ ላይ በትክክል በመሙላትና አባሪ ሰነዶችን ከዲክለራሲዮን ጋር በማያያዝ እንዲሁም ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ሲስተም በማይሰራበት ጊዜ በማንዋል የዋጋ መረጃ ማሳወቂያ ቅጽ በመጠቀም የዋጋ መረጃውን ማቅረብ አለበት፡፡

3/ የጉምሩክ ባለሙያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት በማይኖርበት ጊዜ በማንዋል በቀረበው የዋጋ መረጃ ሰነድ አገልግሎት በመስጠት ሲስተሙ መስራት ሲጀምር በማንዋል ያስተናገዳቸውን ሰነድ ወይም አገልግሎት ወዲያውኑ ወደ መረጃ ቋቱ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

### 23. በጉምሩክ የዋጋ ዝርዝር መረጃ ዲክሌራሲዮን ውስጥ መካተት ያለባቸው መረጃዎች

1/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለዋጋ አወሳሰን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን በመሙላት ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲሆን አቅራቢዉ ስለተፈጸመዉ ግብይት ለማስረዳት የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች ማቅረብ አለበት ፡-

- ሀ) የዲክላራሲዮን አቅራቢዉና ላኪን ጨምሮ በግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ስምና ዝርዝር መረጃ
- ለ) ስለ ዕቃዎቹ የግብይት ሁኔታ፣
- ሐ) በገዢና ሻጭ መካከል ያለውን የግንኙነት ሁኔታና ዓይነት ዝርዝር፣
- መ) የኢንቮይሱ ዋጋ፣ የምንዛሪ ዓይነት፣ የንግድ ስምምነት ዓይነት (INCOTERMS) ፣
- ሠ) ከዕቃው ጋር በተያያዘ በዲክላራሲዮን አቅራቢው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብ ወይም በዓይነት የተከፈሉ ክፍያዎች
- ረ) ከዕቃው በቀጥታ እና ከዕቃው ጋር ከተያያዙ መብቶች ጋር በተገናኘ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ክፍያ
- ሰ) ዕቃውን ለመግዛት የወጡ ሌሎች ወጪዎች፣

ሸ) ከግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ ውጭ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሌሎች የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን በመተመን ለጉምሩክ ካቀረበ የተጠቀመበትን ዘዴ መግለጽ፣

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲሆን አቅራቢዉ የዕቃውን ዋጋ በአግባቡ ለመተመን እንዲቻል የሚከተሉትን መግለጫና መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የዕቃው ሙሉ ስም (የንግድ ሥም ወይም ቴክኒካል ስም)፣

ለ) የዕቃውን አምራች ስም እና የተሰራበት አገር፣

ሐ) የዕቃው ተጨማሪ መግለጫ ( ለምሳሌ፡- ብራንድ፣ ሞዴል ቁጥር፣ ፓርት ቁጥር፣ መጠን፣ ጉልበት)፣

መ) ዕቃውን የተሠራበት ማቴሪያል(ከድብልቅ ማቴሪያል የተሠራ ከሆነ የይዘቱ መቶኛ መጠን)፣

ሠ) የዕቃውን አገልግሎት(ጥቅም) መግለጫ፣

ረ) የመድኃኒት ኬሚካል ስምና ዝርዝር ቴክኒካል መረጃ የሚያሳይ ሰነድ፣

ሰ) የተሽከርካሪ ሥም፣ ዓይነት፣ ሞዴል ቁጥር፣ ምርት ዘመን፣ ሞተር ቁጥር፣ ሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር (ሲሊንደር) ጉልበት፣ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እንደአስፈላጊነቱ ሊብሬ /የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/

ሸ) የኤሌክትሮኒክስ፣ የማሽነሪዎችና መለዋወጫዎች ዝርዝር ማኑዋል እና ቴክኒካል ካታሎግ፣

ቀ) የመለዋወጫ ዕቃዎች ሥም፣ የሚገጠምለት የተሽከርካሪ ዓይነት፣ የአምራች ስም፣ ኦሪጂናል ከሆነ ፓርት ቁጥሩ፣ ኦሪጂናል ካልሆነ የዕቃው አምራች ፓርት ቁጥር እና የኦርጂናል ሪፈረንስ (OEM) ፓርት ቁጥር፣

በ) የዕቃውን ዋጋ ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መግለጫና መረጃዎች፣

## 24. ከጉምሩክ ዝርዝር የዋጋ መረጃ ዲክሌራሲዮን ጋር በአባሪነት ስለሚቀርቡ መረጃዎችና ሰነዶች

በአዋጁ ከአንቀጽ 90 እስከ 96 በተደነገገው መሠረት የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 25 እስከ አንቀጽ 31 የተገለጹትን ዋና ዋና መረጃዎችና ሰነዶችን ጨምሮ ከዕቃ ዲክላራሲዮንና ከዝርዝር የዋጋ መረጃ ዲክላራሱዮን ጋር እንደ አስፈላጊነቱ ለኮሚሽኑ መቅረብ አለበት።



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues No. 1

## 25. በግብይት ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች

1/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በግብይት ዋጋ መሰረት ለመስተናገድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሰነዶችን ከዲክለራሲዮን ጋር አባሪ በማድረግ ማቅረብ ይኖርበታል።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ግዢ ስለመከናወኑ ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የዋጋ ሰነድ (ኢንቮይስ)፣

ለ) በግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ አካላት እና ሚናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ፣

ሐ) ገቢ ዕቃዎቹ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ከመግባታቸው በፊት ዕቃዎቹን ለመግዛት የተገቡ ውሎችና ሥምምነቶች፣

መ) ከዕቃው ግዢ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች (ለምሳሌ፡ የአስመጪነት ፍቃድ፣ የላኪነት ፈቃድ፣ ፕሮፎርማ ኢንቮይስ፣ ፓኪንግ ሊስት፣ የሥሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ የባንክ ፈቃድና ደቢት አድቫይስ፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲና ደረሰኝ፣ የማጓጓዣ ወይም ማስጫኛ ሰነድና ደረሰኝ፣

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ለዕቃው የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ዋጋ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) ከዕቃው ጋር በተያያዘ በዲክላራሲዮን አቅራቢው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብ ወይም በዓይነት የተከፈሉ ክፍያዎች የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣

ለ) ከዕቃው በቀጥታ እና ከዕቃው ጋር ከተያያዙ መብቶች ጋር በተገናኘ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ክፍያን የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣

ሐ) ዕቃውን ለመግዛት የወጡ ሌሎች ወጪዎች የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ዕቃው እስከተጫነበት ወደብ ድረስ የተከፈለ ትራንስፖርትና ኢንሹራንስ ወጪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) ዕቃው የተላከበት (Place of export) ሀገርና ዕቃው በኮንቴነር የታሸገበት ቦታ ማስረጃ፣

ለ) ዕቃው በተላከበት ሀገር ወደብ እስኪደረስ የወጣ የማጓጓዣ ወጪ ማስረጃ፣

ሐ) በዕቃው ግብይት ወቅት ጥቅም ላይ የዋለ ዓለም አቀፍ የንግድ ሥያሜ (INCOTERMS)

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ዕቃው ከተጫነበት ወደብ እስከ መጀመሪያ የኢትዮጵያ መግቢያ በር ድረስ የተከፈለ የማጓጓዣና የኢንሹራንስ ወጪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የማጓጓዣ እና የኢንሹራንስ ሥምምነቱን ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ፣

ለ) ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪዎች ማስረጃ፣

6/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው የኮሚሽን ክፍያዎች ስለመኖራቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የውክልና ስምምነት ሰነድ፣

ለ) የኮሚሽን ክፍያ ዓይነት የሚገልጽ ሰነድ፣

ሐ) የኮሚሽን ክፍያ ኢንቮይስ፣

7/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው የማሸጊያ እና የመያዣ ወጪ ክፍያዎች ስለመኖራቸው እና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) ዕቃውን ለማሸግ የወጣ የማቴሪያል ዓይነትና የጉልበት ወጪ፣

ለ) ዕቃውን የማሸግ ሥራው የተከናወነበት ቦታ ወይም አገር፣

ሐ) ዕቃውን የማሸግ ሥራ ያከናወነው አካል፣

መ) ከዕቃው ተነጥለው የማይታዩ የዕቃ መያዣ ወጪ፣

8/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ለላኪው ያቀረባቸውን ግብዓቶችና አገልግሎቶች ስለመኖራቸውና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) ዕቃውን ለማግኘት ወይም ለማምረት በገዢው በቀጥታ ወይም በገዢው ሥም በሦስተኛ ወገን በኩል ለአምራቹም ሆነ ለላኪው የቀረቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር፣

ለ) ከላይ የተጠቀሱት ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማምረቻ ወጪ ወይም የግዢ ዋጋ እና የማድረሻ ወጪ የሚያሳይ ማስረጃ፣

9/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው የሮያሊቲና ፈቃድ ክፍያዎች ስለመኖራቸውና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-



No. 1
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Finance

ሀ) በዕቃው ግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን አካላት ሚናና ግንኙነት የሚያስረዳ መግለጫ፣

ለ) የሮያሊቲና ፈቃድ ሥምምነት ሰነድ፣

ሐ) የሽያጭ ሥምምነት ሰነድ፣

መ) ከዕቃው ገገር ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች፣

10/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ዕቃዎችን መልሶ ከመሸጥ ከሚገኘው ገቢ ላይ የሚከፈሉ ክፍያዎች ስለመኖራቸውና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የሽያጭ ስምምነት ሰነድ፣

ለ) ገገርው ዕቃውን መልሶ በመሸጥ፣ ለሌላ በማስተላለፍ ወይም በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ ለሻጩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚከፈሉ ክፍያዎች የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣

ሐ) ከዕቃው ገገር ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች፣

11/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ የተሰጠ ወይም የሚሰጥ የቴክኒክ ድጋፍ መኖሩና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የዕቃዎች ወይም የአገልገሎቶች ግገር ውል ሰነድ፣

ለ) ክፍያዎቹ ዕቃዎቹ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለወጡ ወጪዎች የተከፈሉ መሆናቸውን የሚያሳይ መግለጫ፣

ሐ) የተደረገው/የሚደረገው ድጋፍ ዓይነትና ወጪ መጠን ማስረጃ፣

መ)ወጪዎቹ ለዕቃው በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ መካተታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣

12/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ የተከፈሉ የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪዎች መኖራቸውንና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) ዕቃዎች ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የወጣ የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪ መኖሩን የሚያሳይ መግለጫ፣

ለ) የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪውን መጠን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ሐ) የአገልግሎቱን ባህሪና ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ፣

መ) ወጪው ለዕቃው በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ መካተቱን ወይም አለመካተቱን የሚያሳይ ማስረጃ፣

13/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ተቀናሽ የፋይናንስ ወጪዎች መኖራቸውንና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡት እቃዎች ግዥ ጋር በተያያዘ በገዢው የተከፈለውን የብድር ወይም የፋይናንስ ወለድ ክፍያና የክፍያ ስምምነት ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ፣

ለ) ክፍያውን ዘግይቶ እንዲፈፀም የሚያስችሉ ሥምምነቶች የሚያስረዳ ሰነድ፣

14/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክለራሲዮን አቅራቢው ከሻጩ ጋር ግንኙነት ወይም ዝምድና ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) በገዢና ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት ሁኔታና ዓይነት፣

ለ) በገዢና ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት በዕቃው ግብይት ዋጋ ላይ ያለው ተፅዕኖ የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ፣

ሐ) የኮርፖሬቱ(ድርጅቱ) ዝርዝር ፕሮፋይልና የዋጋ ፖሊሲ የሚያሳይ ሰነድ፣

መ) የገዢውን የማከፋፈል ወይም የኤጀንት(ብቸኛ ወኪል) መብት ስምምነት የሚያሳይ ሰነድ፣

ሠ) የዕቃው የሽያጭ የውል ሰነድ እና የሻጩ ኢንቮይስ፣

ረ) በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት በሌላቸው ገዥና ሻጭ መካከል የተከናወነ ሽያጭ (ወደ ኢትዮጵያ የተላኩ) አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣

ሰ) ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ሰነዶች

## 26. <u>በአንድ ዓይነት ዕቃ ዋጋ መሠረት ለመስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1/ በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበትን ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣

2/ ከዕቃው በፊት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎችን በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡ ነጠላ ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ፣

3/ በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎች ማስረጃ፣

4/ የአንድ አይነት ዕቃዎች የአምራች የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር መረጃ(Price List) የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ፣

27. **<u>በተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ መሠረት ለመስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>**

1/ በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ለመስተናገድ የቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክል መሆኑን የሚገልፅ መግለጫ፣

2/ ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ሌሎች ተመሳሳይ ዕቃዎች በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት የተሸጡበትን ነጠላ ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ፣

3/ በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ጊዜ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ተመሳሳይ ዕቃዎች ማስረጃ፣

4/ የተመሳሳይ ዕቃዎች የአምራች የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር መረጃ (Price List) የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ፣

28. **<u>ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ ዋጋን ለመተመን መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>**

1/ በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ለመስተናገድ የቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክል መሆኑን የሚገልፅ መግለጫ፣

2/ በሻጩ ወይም በዲክላራሲዮን አቅራቢው እና በገዢው ወይም በአከፋፋዩ ወይም በቸርቻሪው መካከል ያለውን የዝምድና ሁኔታ እና በዕቃው የሀገር ውስጥ መሸጫ ዋጋ ላይ ያስከተለውን ተጽእኖ የሚያስረዳ ማስረጃ ፣

3/ የሽያጩን ሁኔታ የሚያስረዱ መረጃዎችና ማስረጃዎች፣

4/ ሻጩ ወይም ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዕቃዎቹን የሚሸጥበት ዋጋ ዝርዝር ማስረጃ፣

5/ የሽያጭ ውል ሰነድ ወይም ኢንቮይስ እና ክፍያ የተፈጸመበት ማስረጃ፣

29. **<u>የዕቃውን የጉምሩክ ዋጋ ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ ለመስተናገድ የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች</u>**፡-

1/ የዕቃው ወይም የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ መሸጫ ዋጋ እና የሽያጭ ወጪና ትርፍ ማስረጃ፣

2/ ከዕቃው ጋር በተያያዘ በሀገር ውስጥ የወጡ ወጪዎችና ክፍያዎች ዝርዝር ማስረጃ፣

3/ ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ከመሸጡ በፊት የተከናወነ በምርት ሂደት የታከለ ተጨማሪ እሴት መጠን የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣

4/ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች የሚከፈል የቀረጥና ታክስ መጠን ፣

5/ የዕቃው የንግድ ዘርፍ አማካይ የኮሚሽን ወይም የትርፍ ምጣኔ ወይም የወጪዎችን ምጣኔ የሚያሳይ ማስረጃ፣

6/ የዕቃው የንግድ ዘርፍ አማካይ የማጓጓዣ፣ የኢንሹራንስና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎችን ምጣኔ የሚያሳይ ማስረጃ፣

## 30. በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ የዋጋ ትመና ዘዴ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች

1/ በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ለመስተናገድ የቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክል መሆኑን የሚገልፅ መግለጫ፣

2/ ዕቃዎቹ በላኪው የተመረቱና የተላኩ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣

3/ በላኪው ሀገር ዕቃዎቹን ለማምረት የወጣውን የማምረቻ ወይም የማዘጋጃ ወጪ የሚያሳይ ማስረጃ፣

4/ በላኪው ሀገር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ ወይም የእቃው የንግድ ዘርፍ የመሸጫ፣ የማሸጊያና ሌሎች ወጪዎች እና የትርፍ መጠን ማስረጃ፣

5/ ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማጓጓዝ፣ ለመጫን፣ ለማራገፍ፣ ለመንከባከብ፣ለኢንሹራንስና ለሌሎች ተዛማጅ ስራዎች የተፈፀመ የክፍያ ማስረጃ፣

## 31. ሚዛናዊ የዋጋ ትመና ዘዴ መሰረት በማድረግ ለመስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች፣

1/ በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ለመስተናገድ የቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክል መሆኑን የሚገልፅ መግለጫ፣

2/ የዕቃውን ዋጋ ለመተመን የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ሰነዶች፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ገቢዎች ሚኒስቴር No. 1 Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

## ክፍል ሦስት

## የጉምሩክ ዋጋ ትመና ልማት ዳይሬክቶሬት እና የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

### ምዕራፍ አንድ

### የዳይሬክቶሬቱ፣ የሥራ ክፍሎች እና ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

32. የዳይሬክቶሬቱ ተግባርና ኃላፊነት

1/ የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓትን ማልማት፣ ማሻሻልና ማስተዳደር፣

2/ በኮሚሽኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ዘንድ እና በዳይሬክቶሬቱ ተቀባይነት ያገኙ የዋጋ መረጃዎችን እና ከሌሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካላቸው የዋጋ መረጃ ምንጮች የዋጋ መረጃ መሰብሰብ እና መተንተን፤ የተተነተነውን የዋጋ መረጃ ለአጠቃቀም በሚመች መልኩ ማዘጋጀት ወይም ማደራጀት፤ በዋጋ መረጃ ስርዓቱ የሚገኝ መረጃን ተገቢው ማስተካከያ ማድረግ እና በየጊዜው የዋጋ መረጃ ስርዓቱ ወቅታዊ በማድረግ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተደራሽ እንዲሆን እና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

3/ ከኢንቮይስ በታችና በላይ የሚቀርቡ የዋጋ መረጃዎችንና ማጭበርበሮችን ለመከታተል በየጊዜው ለዕቃዎች ትክክለኛ ዋጋን ማልማት፣ ማደራጀት፣ መወሰን፣ ማስወሰን፣ ማስፈፀም፤

4/ ረቂቅ የዋጋ መመሪያዎችን፣ አሰራሮችን፣ ማንዋሎችን፣ ሰርኩላሮችን በማዘጋጀት ለኮሚሽነሩ ወይም ኮሚሽነሩ ለሚወክለው የስራ ኃላፊ ማቅረብና ሲወሰንም ተግባራዊ ማድረግ፤

5/ በዋጋ አተማመን ዙሪያ የአሰራር ማኑዋል ማዘጋጀት፣ በዋጋ አተማመን ዙሪያ በአዋጅ፣ በመመሪያው በተደነገገው መሠረት እንዲሁም በተዘረጉ አሰራሮች መሠረት በኮሚሽኑ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

6/ ኮሚሽኑን ወክሎ በዋጋ አተማመን ዙሪያ ከተጓዳኝ መ/ቤቶች እና ከሌሎች ሀገራትና የአለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግኑኙነት በመፍጠር የሚገኙ ልምዶችን በማዳበር አስፈላጊ የሆኑ ተሞክሮዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

7/ ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው የዋጋ አተማመን ሥርዓት እየተከተሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በየጊዜው አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

8/ ከቅ/ጽ/ቤቶች እና ከሌሎች የስራ ክፍሎች በዋጋ ትመናና የአሠራር ሥርዓት ዙርያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በጥናት ላይ የተመሠረተ ምላሽ መስጠት፤

9/ ዳይሬክቶሬቱ ከሚያገኘው መረጃዎችና ከሚቀርብለት ሪፖርቶች በመነሳት ሳይሰበሰብ የቀረ ቀረጥና ታክስ መኖሩን አጣርቶ በሚመለከተው ቅ/ጽ/ቤት የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ክፍል አማካይነት እንዲሰበስብ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ እና ድጋፍ መስጠት፣

10/ በዋጋ አተማመን የአሰራር ስርአት ዙርያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለተቋሙ ሰራተኞችና ለሚመለከታቸው አካላት መስጠት፣

11/ ሌሎች ከዋጋ ትመና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት መፈጸም፡፡

## 33. የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት

1/ የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት እና ኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ማቅረቢያ ዲክሌራሲዮን እና ተያያዥ የጉምሩክ ዳታቤዝ ሥርዓቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ፣

ሀ) ዘመናዊ፣ ጥራት ያለው እና ለአጠቃቀም ቀላል እንዲሆን በየጊዜው በመፈተሽ ተገቢው ማሻሻያ ያደርጋል፣

ለ) አገልግሎቱ ሳይቋረጥ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ያደርጋል፣

ሐ) የአጠቃቀሙን ሁኔታ በመገምገም ከዳይሬክቶሬቱ ወይም ከቅ/ጽ/ቤቶች ወይም ከኮሚሽኑ አመራሮች ጋር በመወያየት አስፈላጊው ማሻሻያ ያደርጋል፣

2/ የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ሥርዓትን እና ተያያዥ የጉምሩክ ዳታቤዝ ሥርዓቶች የአጠቃቀም ዝርዝር የአፈጻፀም ማንዋል መሠረት በሚመለከተው የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ወይም በዳይሬክቶሬቱ ወይም በኮሚሽኑ ፈቃድ ያገኙ የሚመለከታቸው ሠራተኞችን በመለየት፣ የመጠቀሚያ መለያና የይለፍ ቃል (ፓስዎርድ) መስጠትና መሰረዝ፣ አስፈላጊው የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት እና መቆጣጠር፣

3/ ከብሔራዊ ባንክ የሚላከውን ሳምንታዊ የገንዘብ ምንዛሪ ልክ በመቀበል በኢትዮጵያ የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት ውስጥ በማስገባት በኮሚሽኑ ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ያሳውቃል፡፡

4/ በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት አጠቃቀም ዙርያ ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመተባበር ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና ቅ/ጽ/ቤቶች ስልጠናና አስፈላጊው ድጋፍ መስጠት፣

5/ ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ ሥርአት በመዘርጋት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

6/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከጉምሩክ ኮሚሽን የስራ ክፍሎች በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት የመረጃ ስርዓቱ የአጠቃቀም ሪፖርቶችን በማውጣት ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች መስጠት

34. **የቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ሃላፊነት**

1/ ኮሚሽኑ የሚያወጣቸው የዋጋ አተማመን መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች እና የአሰራር ሥርዓቶች እንዲሁም የፕሮሲጀር ማንዋሎች በትክክል ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

2/ በኮሚሽኑ የተዘጋጀውን የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ በወጥነት እና በትክክል ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

3/ ለዋጋ መረጃ ቋት በግብአትነት የሚያገለግሉ መረጃዎች እና ከዋጋ መረጃ ዳታቤዝ ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶችና መረጃዎች መዝግቦ በየጊዜዉ ለዳይሬክቶሬቱ ማስተላለፍ፣

4/ የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት እና ኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ ውስጥ የሚገቡትን መረጃዎች ጥራት ለማስጠበቅ የቅርብ ክትትልና የቁጥጥር ሥራ መስራት፤ ከዳይሬክቶሬቱ ወይም ከኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች እንዲስተካከሉ የተላለፉ መረጃዎች መስተካከላቸውን ማረጋገጥና እና ሥራዎች በተቀመጠላቸው የአሰራር ስርዓት ስለመፈፀማቸው የተጠቃለለ ሪፖርት በየወሩ መጨረሻ ለዳይሬክቶሬቱ ማቅረብ፤ ያጋጠሙ ቴክኒካል ችግሮች በመለየትና በማጥናት የመፍትሔ ሀሳብ ማቅረብ፣

5/ የቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ወይም እርሱ የሚወክለው የስራ ኃላፊ የዋጋ ውሳኔ በሚሰጥባቸው የጉምሩክ የስራ ክፍሎች ወይም የስራ ኃላፊዎች የተሰጡ የዋጋ ውሳኔዎች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ውሳኔዎችን ኮሚቴ በማዋቀር ክለሳ የማድረግ፣የማረም፣የማሻሻል፣በትክክለኛ ማስረጃ የተለዩ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለው፤

## **ምዕራፍ ሀለት**

## **የጉምሩክ ባለሙያዎች ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት**

35. **ዋጋ እንዲተምኑና እንዲያለሙ ስልጣን የተሰጣቸው የጉምሩክ ባለሙያዎች የዋጋ ማጣራት እና የመወሰን ስልጣን**

1/ የሰነድ ማረካከቢያና ማረጋገጫ የጉምሩክ ባለሙያ (የፌስቬት ኦፊሰር) አንድ ዲክለራሲዮን ዲክሌር ተደርጎ ለኮሚሽኑ ሲቀርብ የቀረበውን ዲክለራሲዮን የተሟላ

ሰነድ መሆኑን በማረጋገጥ ይረከባል፤ዲክለራሲዮኑ በኮሚሽኑ ካለው የስጋት ደረጃ አንጻር አጣርቶ ለቀጣይ ስራ ለሚመለከተው የጉምሩክ ባለሙያ ያስተላልፋል።

2/ የዋጋ ትመና ልማት ዳይሬክቶሬት በኮሚሽኑ ዋናዉ መ/ቤትና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ያሉ ዋጋ እንዲተምኑና እንዲያለሙ ስልጣን ወይም ኃላፊነት የተሰጣቸው የጉምሩክ ባለሙያዎች ስልጣን፣ ተግባር እና ኃላፊነት አሰራር በማዘጋጀት ለኮሚሽነሩ ወይም ኮሚሽነሩ ለሚወክለው አካል በማቅረብ ያስወስናል፣ሲወሰንም ተግባራዊ ያድርጋል።

## 36. የዋጋ ውሳኔ ኢንስፔክሽን ስርዓት

ዳይሬክቶሬቱ በየደረጃዉ የሚሰጡ የዋጋ ዉሳኔዎች ህግና አሰራርን መሰረት በማድረግ የተወሰኑ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፤ የቅ/ጽ/ቤቶችን የዋጋ ውሳኔና የዋጋ አሰራሮችን ተአማኒነትና ህጋዊነት ለማረጋገጥ በየጊዜው የዋጋ ክለሳ ወይም እንደገና የማየት ወይም የማረም ስራ ይሰራል፤ ስህተት ወይም ጥፋቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ለኮሚሽኑ ሪፖርት ያቀርባል።

## ምዕራፍ ሦስት

## የዲክላራሲዮን አቅራቢዎች ግዴታ እና መብቶች

## 37. የዲክላራሲዮን አቅራቢዎች ግዴታ

1/ በጉምሩክ አዋጅና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን እና የጉምሩክ ዝርዝር የዋጋ መረጃ እንዲሁም ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ አባሪ ሰነዶች ጋር ለጉምሩክ ማቅረብ፤

2/ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ በኮሚሽኑ በኩል በማንዋል ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚዘጋጁ ቅጾች ወይም ሰነዶች ላይ መረጃዎችን በአግባቡ በመሙላት እና ትክክለኛነታቸዉን በማረጋገጥ ለጉምሩክ ማቅረብ፤

3/ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ሞልቶ እና አረጋግጦ ባቀረበዉ መረጃና ሰነድ ላይ ለሚገኝ ማንኛዉም ስህተት ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳል፤

## 38. የዲክላራሲዮን አቅራቢዉ መብቶች

1/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በኮሚሽኑ ወይም በጉምሩክ ባለሙያ ወይም ኦፊሰር የተሰጠውን ውሳኔ በጽሁፍ የማግኘት መብት አለው።

2/ በኮሚሽኑ በተሰጠው የዋጋ ውሳኔ ላይ ያልተስማማ የዲክላራሲዮን አቅራቢ ቅሬታዉን ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ወይም አካል ማቅረብ ይችላል።

## ክፍል አራት

## ሌሎች ድንጋጌዎች

### 39. የገንዘብ ምንዛሪ

የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በየሳምንቱ ረቡዕ ከብሔራዊ ባንክ የሚላከውን ሳምንታዊ የምንዛሬ መጠን በመቀበል በጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት ውስጥ በማስገባት ከሐሙስ ጀምሮ እስከሚቀጥለው ሳምንት ድረስ ተፈፃሚ እንዲሆን ለዳይሬክቶሬቱ እና ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት በፅሑፍ ያሳውቃል።

### 40.የተደራጀ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ አጠቃቀም

1/ ዳይሬክቶሬቱ ወደ ሀገር የሚገቡ እቃዎችን ዋጋ ትክክለኛነት ለማጣራትና ሥጋት ለመወሰን እንዲያስችል በጉምሩክ አዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የጉምሩክ ዋጋ ያደራጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ የመረጃውን ጥራት ይከታተላል።

2/ ለማነፃፀሪያነት የሚውሉ መረጃዎች በዋናነት ለንግድ አላማ በብዛት የገቡ ዕቃዎች ዋጋ ሲሆን የንግድ ዕቃዎች ዋጋ በመረጃ ቋቱ በማይገኝበት ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ተጣርተዉ ወደ መረጃ ቋት የገቡ የአምራች ድርጅቶች ዋጋ በማነፃፀሪያነት ሊያገለግል ይችላል።

3/ በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋት የገቡ መረጃዎችን ከዚህ በታች በተቀመጠው ቅድም ተከተል መሰረት የእቃዎች ዋጋ ዉሳኔ ይሰጣል፡-

ሀ) አውቶማቲክ ሞጁል /ECVS-Automatic Analysis/ ፣

ለ) ኩዌሪ ቢዩልደር ሞጁል /ECVS-Automatic Quiery Builder Moudule/፣

ሐ) አለምአቀፍ ዋጋ ሞጁል/ECVS-International; Price/IP/ ፣

መ) በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ሥርዓት ያልተካተቱ ከዚህ በፊት በየደረጃው ተደራጅተዉ የሚገኙ የዋጋ ዉሳኔዎች፤

4/ የመነሻ ዋጋ የሚወሰንላቸው ዕቃዎች ዋጋ የሚነፃፀረው ቅድሚያ በECVS-International; Price/IP/ ሞጁሉ ላይ በሚገኝ ወቅታዊ የእቃ ዋጋ መረጃ ሲሆን በቅርብ ጊዜ የገባው ዋጋ እንደ መነሻ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 4 የተገለፀው ቢኖርም የመነሻ ዋጋ የሚወሰንላቸው እቃዎች በECVS-International; Price/IP/ ላይ በማይገኝበት ወቅት በECVS-Automatic Quiery

Builder ሞጁል ላይ ያለውን ወቅታዊ ተቀራራቢ አማካኝ ዋጋ በመውሰድ እንደማነፃፀሪያነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

41. <u>የጉምሩክ መረጃ ሚስጥራዊነት</u>

ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ከሚያቀርበው መረጃ በመነሳት ኮሚሽኑ የዋጋ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ጊዜ በዲክላራሲዮን አቅራቢ የሚቀርበውን መረጃ በማጣራት እና የተሟላ በማድረግ ሂደት የሌሎችን ዲክላራሲዮን አቅራቢዎች መረጃ ሚስጢራዊነት መጠበቅ አለበት፡፡

42. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

43. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በነባሩ መመሪያ መሰረት ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

44. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ____________ቀን 2011 ዓ.ም

አዳነች አበቤ

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር